የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 30
ADDIS ABABA - 28th June, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፪/፲፱፻፺፫ ዓ·ም·
የኮቶኑ ስምምነት ማጽደቂያ
አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፭፻፳፰

## CONTENTS

Proclamation No. 242/2001
Cotonou Agreement Ratification
Proclamation ........................................ Page 1528

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፪/፲፱፻፺፫

### የኰቶኑን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የአፍሪካ፣ የካሪቢያንና፣ የፓስፊክ አገሮች በአንድ በኩል፣ እንዲሁም የአውሮፓ ሕብረት አባል አገሮች በሌላ በኩል ሆነው ያደረጉትን የሽርክና ስምምነት እ·ኤ·አ ጁን ፳፫ ቀን ፪ ሺ ኮቶኑ ላይ ስለተፈራረሙ፤

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ የሚውለው የአውሮፓ ሕብረት አባል አገሮች እና ከአካፓ አገሮች ቢያንስ ሁለት ሦስተኛው የማጽደቂያ ሰነዶቻቸውን ከላኩበት ሁለተኛ ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና(፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኰቶኑ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፪/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

እ·ኤ·አ· ጁን ፳፫ ቀን ፪ ሺ ኰቶኑ ላይ የተፈረመው የአካፓ– አውሮፓ የሽርክና ስምምነት ፀድቋል።

### PROCLAMATION No. 242/2001

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE COTONOU AGREEMENT

WHEREAS, Ethiopia is one of the parties to the ACP-EU Partnership Agreement signed in Cotonou, on the 23rd day of June 2000;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force on the first day of the second month following the date of deposit of the instruments of ratification of the Member States and of at least two-thirds of the ACP States;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives has ratified said Agreement at its session held on the 28th day of June, 2001;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Cotonou Agreement Ratification Proclamation No. 242/2001."

2. *Ratification of the Agreement*

   The ACP–EU Partnership Agreement signed in Cotonou, on the 23rd day of June, 2000 is ratified.

፫· <u>የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

*ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ*

*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት*

3. *Power of the Minister of Economic Development and Cooperation*

The Minister of Economic Development and Cooperation is hereby empowered to implement the Cotonou Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 28th day of June, 2001.

Done at Addis Ababa, this 28th day of June, 2001.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE